www.abyssinialaw.com



15ኛ ዓመት ቁጥር 2
15th year No. 2

ባህር ዳር ጥር 18 ቀን 2002 ዓ.ም
Bahir Dar 26th, January, 2010

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ዝክረ-ሕግ

# ZIKRE-HIG OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA



| | | | |
|---|---|---|---|
| የአንዱ ዋጋ ብር 11.62 Price Birr | በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | ISSUED UNDER THE AUSPICES OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE | የፖ.ሣ.ቁ. 312 P.O.Box |



| ማውጫ | CONTENTS |
|---|---|
| ደንብ ቁጥር 71/2002 ዓ.ም በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የመንገድ ሥራዎች ድርጅት ማቋቋሚያ፣ ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ | Regulation No. 71/2010 The Amhara National Regional State Road Works Enterprise Establishment and Determination of its powers and Duties, Council of Regional Government |

## ደንብ ቁጥር 71/2002 ዓ.ም

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የመንገድ ሥራዎች ድርጅትን ለማቋቋምና፣ ሥልጣንና ተግባራቱን ለመወሰን የወጣ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ

## Regulation No. 71/2010

A COUNCIL OF REGIONAL GOVERNMENT REGULATION ISSUED FOR THE ESTABILISHMENT AND DETERMINATION OF ITS POWERS AND DUTIES OF THE ROAD WORKS ENTERPRISE IN THE AMHHARA NATIONAL REGIONAL STATE.

www.abyssinialaw.com


## መቅድም

አዳዲስ የመንገድ ግንባታ፣ የነባር መንገዶች ጥገና፣ የመንገዶችን ደረጃ የማሳደግና ማሻሻል ሥራዎች እንዲሁም ሌሎች ተዛማጅ የሲቪል ወርክ ሥራዎችን ለመፈፀም የሚችል ጠንካራ የመንገድ ሥራዎች ኢንተርፕራይዝ ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

ውጤታማና ትርፍ ያለው እንዲሁም ደረጃውን የጠበቀ የመንገድ ሥራዎች ለማካሄድና ለመንገድ እና ሌሎች የኮንስትራክሽን ሥራዎች አስፈላጊ የሆኑ የግንባታ ማሽነሪዎችን ለተገልጋዩ በተመጣጣኝ ዋጋ የኪራይ አገልግሎት ለመስጠት አቅም ያለው ኢንተርፕራይዝ ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

ከላይ የተጠቀሱትን ተግባራት በጥራት ማካሄድና ራሱን የቻለ መንግስታዊ የልማት ድርጅት ማቋቋም ተገቢ በመሆኑ፣

የአማራ ብሔራዊ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት በተሻሻለው የክልሉ ህገ መንግስት አንቀጽ 58 ንዑስ አንቀጽ 2 እና ንዑስ አንቀጽ 7 ድንጋጌዎች ሥር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

## PREAMBLE

WHEREAS, it has been necessary to establish a strong road works enterprise whereby it may enable itself to perform activities of new road constructions, maintenance of existing roads and upgrading and improving of roads as well as accomplishes other civil-work related activities thereof;

WHEREAS, it has been necessary to establish an enterprise having a capacity to undertake effective, profitable as well as standardized road works and to provide rent services of required construction machineries to the service seekers on reasonable price thereof;

WHEREAS, it has been appropriate to establish an autonomous government Enterprise and thereby to effectively undertake the aforementioned duties thereof;

Now, therefore, the Amhara National Regional Government, in accordance with the powers vested in it under the provisions of Article 58 sub-Articles 2 and 7 of the Revised Constitution of the National Regional State, hereby issues this regulation.

www.abyssinialaw.com


# ክፍል አንድ
# ጠቅላላ

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የአማራ መንገድ ሥራዎች ድርጅት ማቋቋሚያ ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 71/2002" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 2. ትርጓሜ፣

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚሁ ደንብ ውስጥ፦

1. "ድርጅት" ማለት በዚህ ደንብ የተቋቋመውን የአማራ መንገድ ሥራዎች ድርጅት ነው።
2. "የመንገድ ሥራዎች" ማለት አዲስ የመንገድ ግንባታዎች፣ የነባር መንገድ ጥገና፣ የመንገዶችን ደረጃ የማሳደግና የማሻሻል ሥራዎች ማለት ነው።
3. "ቦርድ" ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ 8 መሠረት የተቋቋመ የአማራ መንገድ ሥራዎች ድርጅት የሥራ አመራር ቦርድ ነው።

# PART ONE
# GENERAL

## 1. Short Title

This regulation may be cited as "The Amhara Road Works Enterprise Establishment and Determination of Powers and Duties, Council of Regional Government Regulation No.71/2010."

## 2. Definition

Unless the context otherwise requires, in this regulation:

1. "Enterprise" shall mean the Amhara Road Works Enterprise established under this regulation hereof;
2. "Road Works" shall mean activities of constructions of new roads, maintenance of existing roads and upgrading and improving of grades of roads.
3. "Board" shall mean a managing board of the Amhara Road Works Enterprise established pursuant to Article 8 of this regulation hereof.

www.abyssinialaw.com


# ክፍል ሁለት

## ስለ ድርጅቱ መቋቋም፣ ተጠሪነት፣ ድርጅታዊ አቋም እና ዓላማዎች

### 3. ስለ ድርጅቱ መቋቋምና ተጠሪነት፣

1. የአማራ መንገድ ሥራዎች ድርጅት /ከዚህ በኋላ "ድርጅቱ" እየተባለ የሚጠራ/ ራሱን የቻለና ህጋዊ ሰውነት ያለው ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. ድርጅቱ የተቋቋመው ላልተወሰነ ጊዜ ሆኖ ተጠሪነቱ ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድርና በር/መስተዳድሩ የሚሰየሙ አባላት ላሉት የሥራ አመራር ቦርድ ይሆናል።

### 4. የድርጅቱ ዋና ጽ/ቤት

1. የድርጅቱ ዋና ጽ/ቤት ባህር ዳር ከተማ ነው።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ድርጅቱ እንደአስፈላጊነቱ በማንኛውም ቦታ የሚቋቋሙ ቅርንጫፍና የፕሮጀክት ጽ/ቤት ሊኖሩት ይችላሉ።

# PART TWO

## ESTABLSHMENT, ACCOUNTABILITY, ORGANIZATIONAL STRUCTURE AND OBJECTIVES OF THE ENTERPRISE

### 3. Establishment And Accountability of the Enterprise

1. The Amhara Road Works Enterprise, /hereinafter referred to as "The Enterprise"/, is hereby established as an autonomous Enterprise having its own legal personality under this regulation.
2. The Enterprise shall be established for indefinite period of time and be accountable to the Head of the Amhara National Regional State and to the managing board having members to be designated by the Head of the Regional Government.

### 4. Head Office of the Enterprise

1. Head Office of the Enterprise shall be in Bahir Dar.
2. Without prejudice to the provision of sub-art 1 of this Art., the Enterprise may, as deemed necessary, have branches and project offices to be established at any place thereof,

www.abyssinialaw.com


## 5. ድርጅታዊ አቋም

ድርጅቱ ከዚህ በታች የተመለከቱት አካላት ይኖሩታል፣

1. የሥራ አመራር ቦርድ
2. በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር የሚሾሙ አንድ ዋና ሥራ አስኪያጅና ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጆች፣ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል።
3. ሌሎች በየደረጃው የሚያስፈልጉ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ፣ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል።
4. የሠራተኞች ቅጥርና የክፍያ ሁኔታን አስመልክቶ በመመሪያ የሚወሰን ይሆናል።

## 5. Organizational Structure

The Enterprise shall have organs specified herein below:

1. A managing board;
2. A General Manager and vice Managers to be appointed by the Head of the Regional Government. Particulars shall be determined by a directive.
3. Other heads and staff necessary at all levels. Particulars shall be determined by a directive.
4. With regard to recruitment and payment of the employees shall be determined by a directive.

## 6. የድርጅቱ ዓላማዎች፡-

ድርጅቱ ከዚህ በታች የተመለከቱት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1. የመንገድ ሥራዎችን በጥራት፣ በተቀላጠፈና ውጤታማ በሆነ መንገድ በማከናወን በክልል እና በሀገር አቀፍ ደረጃ ለሚካሄዱ የልማት ሥራዎች ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣
2. ለክልሉና ለሀገር የኢኮኖሚ እድገት እና ለሕዝቡ ኑሮ መሻሻል ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር የመንገድ የመሠረተ ልማት እንዲስፋፋ ማድረግ፣
3. የግንባታ ጥራታቸውን የጠበቁና ኢኮኖሚያዊ የሆኑ የመንገድ ሥራዎችን በማከናወን የድርጅቱ ህልውና እንዲረጋገጥ መስራት፣

## 6. Objectives of the Enterprise

The Enterprise shall have the following objectives specified herein below:

1. To create conducive situation for development activities to be undertaken in the regional and national levels by carrying out road works in quality and in an efficient and effective manner thereof.
2. To cause the expansion of road infrastructure that creates conducive situation for the regional and national economic growth and improvement of the people's livelihood.
3. Having carried out road works which maintain their construction qualities and are economical thereof, to work so as to be realized the existence of the enterprise;

www.abyssinialaw.com


4. አዳዲስ የመንገድ ግንባታ፣ የነባር መንገዶች ጥገና፣ የመንገዶችን ደረጃ የማሳደግና ማሻሻል ሥራዎች አገልግሎት በጥራት በመስጠት የክልሉን የመሠረተ ልማት ችግሮች መፍታት፣
5. እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች ተመሳሳይ የመንገድ ሥራ ተግባራትን ማከናወን፣

## ክፍል ሦስት
## የድርጅቱ ሥልጣንና ተግባር

### 7. የድርጅቱ ሥልጣንና ተግባር

ድርጅቱ ከዚህ በታች የተመለከቱት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ለመንግስት የልማት ፖሊሲ ቅድሚያ ትኩረት በመስጠት በመንግስት በሚሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በድርድር እና በጨረታ አግባብ መንገዶችንና ድልድዮችን መገንባት፣ ማሻሻልና መጠገን፣ ከዘርፉ ተገልጋዮች የሚቀርቡ የመንገድ እና የግንባታ ሥራዎችን ማከናወን፣
2. የግንባታ ዕቃዎችንና መሳሪያዎችን ማከራየት፣
3. ለመንገድና ሌሎች የግንባታ ሥራዎች አስፈላጊ የሆኑ የተለያዩ የግንባታ መሳሪያዎች እና ቁሳቁሦች ማምረት፣ ከውጭ አገር ማስመጣት፣ መሸጥ እና ማከራየት፣

4. To solve problems of the regional infrastructure by effectively providing activities of service of new road construction, maintenance of existing roads and upgrading and improving of roads' grade;
5. Perform such other similar road work activities, as deemed necessary.

## PART THREE
## POWERS AND DUTIES OF THE ENTERPRISE

### 7. Powers and Duties of the Enterprise

The Enterprise shall have the following powers and duties specified herein below:

1. Construct, improve and maintain appropriate roads and bridges, in negotiation and at auction, upon the order of the Regional State by giving prior attention to the government development policy; carry out road and construction works to be submitted to it from the sartorial service seekers;
2. Rent out goods and materials of construction,
3. Produce various construction materials and tools necessary for road and other construction works; import same from foreign country, sell and lease out same thereof;

www.abyssinialaw.com


4. የመንገድ ዘርፍ አቅም ግንባታ ሥራዎችን ያከናውናል፣ የመሳሪያ ኦፕሬተር እና ሌሎች ተዛማጅ የሥልጠና ፕሮግራሞች ይቀርፃል፣ በሥራ አመራር ቦርድ ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል።
5. ለደንበኞች ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት አስፈላጊ የሆኑ የግንባታ ፕሮጀክቶችና ቡድኖች እንደየሁኔታው ያቋቁማል።
6. ውል ከገባባቸው የግንባታ ሥራዎች ለሌሎች የሥራ ተቋራጮች የተወሰነውን የሥራ ክፍል እንዲሰሩ ሊዋዋል ይችላል።
7. ሕግ በሚፈቅደው መሠረት በኢንቨስትመንት ሥራዎች ተሣታፊ ይሆናል።
8. ለሚያከናውናቸው ሥራዎች እና ለሚሰጠው አገልግሎት ተገቢውን ክፍያ ይሰበስባል።
9. ኢኮኖሚያዊ የሆነ እና የነፃ ገበያ አሠራርን ባገናዘበ መልኩ የድርጅቱን የፋይናንስ፣ የሰው ሃይል እና የማሽነሪ አጠቃቀም የአሠራር ስርዓት/ፖሊሲዎች/ ሃሣብ ያመነጫል ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል።
10. በአክስዮን ገበያ ይሳተፋል።
11. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያግዙ ሌሎች ተዛማጅ አገልግሎቶች እና ሥራዎችን ያከናውናል።

4. Carry out the road sector capacity building activities; formulate device operator and other related training programs; and implement same up on approval of the managing board;
5. Establish necessary construction projects and teams as the circumstance may be with the view to providing efficient service to customers therein;
6. May enter into contract with other work contractors on certain parts of work to be undertaken thereof, among from the construction works to which it has already entered into therein.
7. Shall be active participant in investment activities in line with law,
8. Collect appropriate charges for the activities it may perform and the service it may render therein;
9. with respect to economical and free-market working system, initiate a proposal of working procedure/policies/ in terms of finance, human resource and machinery management of the Enterprise and implement same up on approval;
10. Participate in share-company market;
11. Perform such other related services and activities helpful for the attainment of its objectives thereof.

www.abyssinialaw.com


## ክፍል አራት
## የድርጅቱ የሥራ አመራር ቦርድ አደረጃጀት፣ ተጠሪነት፣ ሥልጣንና ተግባር

### 8. የሥራ አመራር ቦርድ አባላት አደረጃጀትና የሥራ ዘመን

1. የሥራ አመራር ቦርዱ ከአምስት እስከ ሰባት የሚደርሱ አባላት ይኖሩታል።
2. የቦርዱ አባላት በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ይሰየማሉ።
3. ቦርዱ ሰብሳቢና ፀሐፊ ይኖሩታል፣
4. የቦርዱ እና የአባላቱ የሥራ ዘመን በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር የሚወሰን ይሆናል።
5. የቦርዱ አባላት ጥቅማጥቅም በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት እንደአስፈላጊነቱ ይወሰናል።
6. የቦርዱ ተጠሪነት ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ይሆናል።

### 9. የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር

ቦርዱ በዚህ ደንብ መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖታል፦

## PART FOUR
## ORGANIZATION, ACCOUNTABILITY, POWERS AND DUTIES OF ENTERPRISE'S BOARD

### 8. Organization and Term of Office of Board's Members

1. The managing board shall have members numbering from five to seven.
2. The members of the board shall be designated by the Head of Regional Government.
3. The board shall have a chair-person and a secretary;
4. The term of office of the board and its members hall be determined by the Head of the Regional Government
5. Benefits of the board members shall, as deemed necessary, be determined by the Council of the Regional Government.
6. The accountability of the board shall be to the head of the Regional Government.

### 9. Powers and Duties of the Board

The board shall, pursuant to this regulation, have the following powers and duties:

www.abyssinialaw.com


1. ድርጅቱ የሚመራበትን አጠቃላይ ፖሊሲ በማመንጨት ለመስተዳድር ምክር ቤት አቅርቦ ያፀድቃል፣ በተግባር ላይ መዋሉን ይከታተላል።
2. ድርጅቱ የሚመራባቸውን ልዩ ልዩ ደንቦችና መመሪያዎች ያወጣል።
3. የድርጅቱን የሥራ ዕቅድና በጀት መርምሮ ያፀድቃል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል።
4. የድርጅቱ ንብረት በአግባቡ የተያዘ መሆኑን፣ የሰው ሃይል እና የገንዘብ አጠቃቀሙ የክልሉን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት ግቦች እንዲሁም የድርጅቱን ዓላማዎች ለማሳካት ብቁ መሆኑን ያረጋግጣል።
5. ድርጅቱ በሰው ኃይል፣ በማሽነሪ እና በሥራ አመራር የሚጠናከርበትን እንዲሁም ሁለንተናዊ የመፈፀም አቅሙ የሚያድግበትን መንገድ ያስጠናል፣ ጥናቱ ጠቃሚ ሆኖ ሲያገኘው ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል።
6. የድርጅቱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በክልሉ ዋና ኦዲተር ወይም በውጭ ኦዲተር እንዲመረመር ያደርጋል።
7. የድርጅቱን ካፒታል በመቀነስ ወይንም በመጨመር ውሣኔ ያሳልፋል።

1. Initiate and submit the general policy in which the enterprise is to be managed to the council of the Regional Government and cause the approval of same; follow up the implementation of same;
2. Issue various regulations and directives in which the enterprise is to be directed therein;
3. Review and approve the working plan and budget of the enterprise; monitor its implementation thereof;
4. Ensure that property of the enterprise is properly handled; its human resource and finance management is efficient to attain economic and social development goals of the Region and objectives of the Enterprise therein.
5. Cause the study of a way through which the enterprise may be strengthened in terms of human resource, machinery and management and its overall execution capacity may grow thereof; cause the implementation of same wherever it finds the study useful;
6. Cause the audit of the books of account and finance-related documents by the office of the Auditor General of the Regional State or by external auditor.
7. Pass a decision of reducing or increasing the capital of the Enterprise thereof,

www.abyssinialaw.com


8. የድርጅቱን ዋና ሥራ አስኪያጅና ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጆች ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቅርቦ ያሾማል።
9. ለዋና ሥራ አስኪያጁ ተጠሪ የሆኑ የሥራ ሂደት መሪዎችን ምደባ ያፀድቃል፣ የቦርዱን ፀሐፊም ይሰይማል፣
10. የቦርዱን መተዳደሪያ ውስጠ ደንብ ስነ-ሥርዓት ቀርፆ ተግባራዊ ያደርጋል።
11. ወቅታዊ ሪፖርቶችን ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት እና ለርዕሰ መስተዳድሩ ያቀርባል።

## 10. የቦርዱ የስብሰባ ስርዓት

1. ቦርዱ በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያካሂዳል። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያካሂድ ይችላል።
2. ከቦርዱ አባላት አብላጫው በስብሰባው ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።
3. የቦርዱ ውሣኔዎች በድምፅ ብልጫ የሚያልፉ ሲሆን፣ የአባላቱ ድምፅ እኩል በኩል የተከፈለ ከሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ስነሥርዓት ሊያወጣ ይችላል።

8. Nominate General Manager and Vice General Managers of the Enterprise and submit them to the Head of the Regional Government to be so appointed.
9. Approve the assignment of Process Owners accountable to the General Manager; designate the secretary of the board thereof;
10. Formulate and implement administrative guide-lines of internal working procedures of the board.
11. Submit periodic reports to the Council of Regional Government and to the head of Regional Government.

## 10. Meeting Procedure of the Board

1. The board shall convene regular meeting once in a month; provided, however that wherever it is found necessary, it may hold an extraordinary meeting at any time.
2. There shall be a quorum where majority of members of the board show up at the meeting.
3. Decisions of the board shall be passed through a majority vote; provided, however, that in case of a tie, the chair-person shall have a casting vote.
4. Without prejudice to provisions of this Art. Hereof, the board may issue its own meeting procedure.

www.abyssinialaw.com


## ክፍል አምስት
## ስለ ሥራ አስኪያጁ ሥልጣንና ተግባር

### 11. የዋና ሥራ አስኪያጁ ሥልጣንና ተግባር

የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የድርጅቱን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፣
2. የድርጅቱን ጽ/ቤት ያደራጃል፣ የድርጅቱን የሥራ መዋቅር፣ የሠራተኞችን ደመወዝና አበል እያዘጋጀ ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣
3. የድርጅቱን ሂሣብ ለማንቀሳቀስ የባንክ አካውንት ይከፍታል፣
4. የድርጅቱን የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ ዕቅድ፣ በጀትና ፕሮግራም እያዘጋጀ ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል።
5. ተጠሪነታቸው ለዋና ሥራ አስኪያጅ የሆኑ የድርጅቱን የሥራ ኃላፊዎች ቅጥር ምደባና ስንብት በተመለከተ ለሥራ አመራር ቦርዱ በማቅረብ ያስፀድቃል።
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብነት ባለው ህግና በድርጅት የአስተዳደር ደንብ መሠረት ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሳድጋል፣ ያሰናብታል፣

## PART FIVE
## POWERS AND DUTIES OF THE MANAGER

### 11. Powers and Duties of the General Manager

The General Manager of the Enterprise shall have the following powers and duties:

1. Direct, administer and supervise over activities of the Enterprise;
2. Organize the office of the Enterprise, prepare its working structure, salary and allowance of employees, submit same to the board and follow up its implementation upon approval;
3. Open bank account of the Enterprise in order to operate account of same;
4. Prepare the short, medium and long-term plan, budget and program of the Enterprise, submit same to the board and put into effect upon approval;
5. Submit to and have appointed by the board the recruitment, assignment and dismissal of the Enterprise's work heads accountable to him ;
6. Without prejudice to the provision of sub-Art.5 of this Art. Hereof, recruit, administer, promote and dismiss employees, pursuant to pertinent law and administrative rules of the enterprise;

www.abyssinialaw.com


7. ለድርጅቱ በተፈቀደለት በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጭ እንዲሆን ያደርጋል፣ በሥራ ላይ መዋሉንም ይቆጣጠራል፣
8. የቦርዱን ውሣኔ ይፈፅማል፣ ያስፈፅማል፣
9. ድርጅቱ ከሚሰጠው አገልግሎት የሚገኘው ገቢ በአግባቡ መሰብሰቡን ይቆጣጠራል፣
10. ድርጅቱ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርገው ግንኙነትና ውለታ ሁሉ መስሪያ ቤቱን ይወክላል፣
11. የየሩብ ዓመቱን የሥራ አፈፃፀም እና የሂሣብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሥራ አመራር ቦርዱ እና ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ያቀርባል፣
12. በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል

## 12. የምክትል ሥራ አስኪያጆች ሥልጣንና ተግባር

1. በዋና ሥራ አስኪያጁ ተለይተው የሚሰጡ ተግባራትን ያከናውናሉ፣
2. ዋና ሥራ አስኪያጁ በማይኖርበት ወይም ሥራውን ማከናወን በማይችልበት ጊዜ በዋናው ሥራ አስኪያጅ የሚወከለው ተተክቶ ይሠራል።

7. Cause the withdrawal of money in accordance with budget appropriated to the enterprise and working program and thereby supervise over its implementation thereof;
8. Implement and cause the implementation of decisions of the board;
9. Supervise over that the income to be obtained from the service provided by the enterprise is properly collected thereof;
10. Represent the office in all relations and contract that the enterprise may undertake with the third parties;
11. Prepare and submit to the board and to the head of Regional Government quarterly performance and account reports;
12. Perform such other duties as may be assigned to him by the board.

## 12. Powers and Duties of Vice Managers

1. Perform duties specifically given to them by the General Manager.
2. One who is specifically delegated by the General Manager act on behalf of the General Manager in the absence or under the circumstances where he is unable to perform his normal duties.

www.abyssinialaw.com


# ክፍል ስድስት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## ስለድርጅቱ መነሻ ካፒታል እና የበጀት ዓመት

### 13. የድርጅቱ መነሻ ካፒታል

1. የድርጅቱ መነሻ ካፒታል ብር 500,000,000.00 (አምስት መቶ ሚሊዬን) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 5,000,000.00 (አምስት ሚሊዬን ብር) በጥሬ ገንዘብ እና ብር 186,712,353.43 (አንድ መቶ ሰማንያ ስድስት ሚሊዬን ሰባት መቶ አሥራ ሁለት ሽህ ሦስት መቶ አምሳ ሦስት ብር ከአርባ ሦስት ሳንቲም) በዓይነት ተከፍሏል።
2. የድርጅቱ የበጀት ዓመት ከክልሉ መንግስት የበጀት ዓመት ጋር አንድ ነው።

### 14. የሂሣብ መዛግብት

1. ድርጅቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብትን ይይዛል፤
2. የድርጅቱን የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች አያያዝ በተመለከተ በቦርዱ ተቀባይነት ያላቸው የሂሣብ አሠራሮች ሥራ ላይ እንዲውሉ ሊያደርግ ይችላል፣ ዝርዝሩም በመመሪያ ይወሰናል።

# PART SIX

# MISCELLANEOUS PROVISIONS

## INITIAL CAPITAL AND FISCAL YEAR OF THE ENTERPRISE

### 13. Initial Capital of the Enterprise

1. The initial capital of the enterprise is Birr 500,000,000.00 (Five hundred Million Birr) and out of this Birr 5,000,000.00 (Five Million Birr) and 186,712,353.43 (One hundred eighty six million, seven hundred twelve thousands & three hundred fifty three and forty three cents) in cash and kind respectively is disbursed thereof.
2. The fiscal year of the enterprise shall be that of the Regional State.

### 14. Books of Account

1. The Enterprise shall keep complete and accurate books of account.
2. The board may cause the operation of an acceptable accounting system as of regards the maintenance of books of account and finance-related documents of the Enterprise. The particulars shall be determined by a directive.

www.abyssinialaw.com


## 15. የሂሣብ ምርመራ

የድርጅቱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በክልሉ ዋና ኦዲተር መ/ቤት ወይም ቦርዱ በሚሰይማቸው የውጭ ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራል።

## 16. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ታይቶና ተመርምሮ ከፀደቀበት ጥር 18 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባህር ዳር

ጥር 18 ቀን 2002 ዓ.ም

አያሌው ጐበዜ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ርዕሰ መስተዳድር

## 15. Auditing

The Books of account and financial as well as property related documents of the enterprise shall be audited yearly by the Office of the Auditor General of the Regional State or by the External Auditors to be assigned by the board.

## 16. Effective Date

This regulation shall come into force as of the date of its review and ratification by the council of the Regional Government

Done at BahirDar

This 26th day of January, 2010

Ayalew Gobezie

Head of Government of the Amhara

National Regional State